# አስራትን ስንዘክር

አገሬ ከስዊድን
2018-05-12

ኢትዮጵያ ቀን ጥሏት፤ በባንዶች እጅ ወድቃ
ህዝቡ በሰመመን፤ ሲያሸልብ ሳይነቃ
አንድ የቁርጥ ቀን፤ ልጅ አስራትን አግኝታ
ላመነበት ነገር፤ የማያመነታ
የሀገር መድህኒት፤ የወገን አለኝታ
በባንዶች ቅንብር፤ ተጠቃ ተመታ።

ባንዳው የባንዳው ልጅ፤ ጨብጦ ስልጣን
ኢትዮጵያን ሲያደማ፤ ሲያጠፋ አማራን
አንድነት ሲናጋ፤ በዘር ሲለየን
ብቸኛ ጠበቃ፤ አስራት ነበረን።

አስራት ምን ባጠፋ፤ መከራ ተጋተ
ጀግንነት ስላለው፤ በአያቱ የባተ
ከአገር በፊት ወጥቶ፤ ስለተሟገተ
ግዞት ጥሪው ሆኖ፤ በመለስ ታገተ።

አስራት ምን ባጠፋ፤ ለሞት ተዳረገ
የክብር ሞት መሞት፤ ባህል ስላረገ፤
አገሩን ወገኑን፤ በነፍሱ ታደገ።

ፕሮፌሰር አስራት፤ የአገር መድህኒት
ስንቱን በጥበቡ፤ ቀዶ ፈውሶት
እንደ ውድ አባቱ፤ እንደ ሰማዕት
እሱም በባንዶች ግፍ፤ አልፏል በፅናት።

ከአባቱ ከአያቱ፤ ኖሮት ማስተዋል
በዋልጌዎች ጥፋት፤ በባንዶች ተንኮል
አልገዛም ብሎ፤ አሻፈረኝ ቢል
ዳኝነት ቢጠፋ፤ ፍርድ ቢጓደል
አስራት ለሀገሩ፤ መስዋዕት ሆኗል።

አስራትን አድናቂ፤ አወዳሽ አክባሪ
ባለ አደራው ትውልድ፤ አስራትን ዘካሪ
ለአንድነት አሳቢ፤ ለአገር ተቆርቋሪ
ፈለገ አስራት ይሁን የእያንዳንዱ ጥሪ።

አስራትን ስንዘክር፤ ሰንጠራ ስሙን
ቃል መግባት አለብን፤ ልንይዝ አርማውን።

የአስራትን ስንዘክር፤ ተሰልፈን በአንድ
ቆርጠን እንነሳ፤ ሳንንገዳገድ።
የአስራትን ፈለግ፤ ይዘን ለመንጎድ።

አስራት ለድንበሩ፤ አስራት ለአንድነቱ
አስራት አስተዋዩ፤ ለሰብአዊነቱ
በማተቡ ፀንቶ፤ እንቢ በማለቱ
ከፍሏልና ነፍሱን፤ እንደ አባት አያቱ።

እኛም የሱ ልጆች፤ በእሱ የምንኮራ
የውሻ ሞት ሲሞት፤ በኢትዮጵያ አማራ
ባይተዋር አንሁን፤ ጠላት ሲያንሰራራ
ቆርጠን እንቀበል፤ የአስራትን አደራ።

መሞትም ካለብን፤ እንሙት በኩራት።
ለሀገር ለወገን፤ ቆመን በፅናት።